# ዜና

## ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር በተያያዘ የታሰሩት የፍርድ ቤት ውሎ ሪፖርታዥ

## «ግንቦት 7፣ እንደነ አል-ሻባብና አል-ኢትሀድ ለእኛ ከባድ ፈተና አይደለም»

**ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ**

***«እስረኞቹ በፖሊስ መኪና ለ18 ጊዜ ፍ/ቤት ተመላልሰው ማንም ሳያያቸው በድብቅ ሄደዋል:: እንደደዚህ አይነት ነገር ገጥሞኝና አይቼ አላውቅም...»***

***የቢቢሲ ጋዜጠኛ***

ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው የታሰሩት ትላንት በአራዳ ምድብ ችሎት ከቀኑ 7:45 ቀርበዋል:: በዕለቱም ከ250-300 የሚጠጉ የእስረኞች ቤተሰቦችና ጓደኞች እንዲሁም ብዛት ያላቸው ጋዜጠኞች ተገኝተው ነበር:: ከ7:30 ጀምሮ የፌዴራል ፖሊሶች በፍ/ቤቱ የተገኙ ሰዎችን እና ጋዜጠኞችን በአራዳ ፍ/ቤት ዋና መግቢያ ደረጃ ላይ እንዲሰባሰቡ ትዕዛዝ ሰጡ:: በዋና መግቢያ ደረጃ እና በችሎቱ መካከል ያለውን ክፍት ቦታ ማንም ሰው እንዳይገኝበት በማድረግ መሣሪያ የያዙ ፖሊሶች ብቻ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቆመዋል:: 7:45 ገደማ ሽራ የለበሱ ፒክ አፕ የፖሊስ መኪኖች እስረኞችን በተናጠል፤ በአንድ አንድ መኪና እጃቸውን እንደታሰሩ በማምጣት ማንም እንዳያያቸው መኪናው ወደኋላ (ወደችሎቱ) በማስጠጋት ፍርድ ቤት እየገቡ በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ ይዘዋቸው የመጡትን ይዘዋቸው ተመልሰዋል:: ከ7ኛ መኪና በኋላ በአንድ አንድ መኪና ውስጥ ከ2 እስከ 4 (በግምት) የሚደርሱ እስረኞችን በአጠቃላይ ለ18 ጊዜ ያህል ፍርድ ቤት አመላልሰዋቸዋል:: በእነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ ማንም ቤተሰብም ሆነ ጋዜጠኛ እስረኞችን የማየት እድል አልገጠመውም:: የእስረኛ ቤተሰቦች ለአንድ ወር ያህል ታሳሪዎችን ለማየት ጥረት ቢያደርጉም እንዳልተሳካላቸው ገልጸውልናል:: አንዳንዶች በዚህ የተነሳ አምርረው ሲያለቅሱም ተስተውለዋል::

በችሎቱ ገብተው የወጡት ታሳሪዎች ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ በችሎቱ የቆዩ ሲሆን በ17ኛው መኪና የመጡት ታሳሪ ግን ለ20 ደቂቃ (ከሌሎቹ ረዘም ላለ ጊዜ) ያህል በችሎቱ ቆይተው ወጥተዋል::

የመጨረሻዎቹ እስረኞችም 9:45 ገደማ ከፍ/ቤቱ ጨርሰው ሄደዋል። ከችሎቱ የወጡት የእስረኞቹ ጠበቃ ለጋዜጠኞቹ እንደገለጹት የፖሊስ ምርመራ ተጠናቅቋል፤ ቀጠሮውም ለሰኔ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ተይዟል በማለት ተጨማሪ ነገር ከመግለጽ ተቆጥበዋል።

በፍ/ቤቱ የቢ.ቢ.ሲ፣ የኤ.ኤፍ.ፒ፣ የሮይተርስ፣ የቪኦኤ እንዲሁም ጥቂት የግል ጋዜጠኞች እና የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ተገኝተው ነበር። አውራምባ ታይምስም የቢ.ቢ.ሲ ጋዜጠኛዋን ስለሁኔታው ጠይቋት «እንደዚህ አይነት ነገር ገጥሞኝ እና አይቼ አላውቅም፤ እውነት ይሄ ነገር ትክክል ነው? ለምን እስረኞቹን በድብቅ እና በሚስጥር ሊያስገቧቸው ቻሉ? ...» በማለት በግርምት ገልጻለች። የእስረኛ ቤተሰቦችም ሁሉም ለአንድ ወር ያህል እስረኞችን በዓይን ማየት አለመቻላቸውን በሀዘን ገልፀዋል። «የምናቀርብላቸውን ስንቅም በትክክል ይድረሳቸው አይድረሳቸው የምናውቀው ነገር የለም» ያሉት ደግሞ የሌተናል ኮሎኔል ደምሰው አንተነህ ባለቤት እና የባለቤታቸው እናት ናቸው። «መኖሪያችን ሃረር ነው ከሃረር ለስድስት ጊዜ ያህል ተመላልሰን መጥተናል፤ ግን በአይን ልናየው አይቻልንም» ብለዋል።

ወ/ሮ ኑኑዬ የተባሉ የአቶ ጽጌ ኃብተማርያም(የአቶ አንዳርጋቸው አባት) ልጅ በበኩላቸው «ህገ መንግስቱ የፈቀደልንን እስረኞችን የመጎብኘት መብታችንን ተነፍገናል። ለአንድ ወር ያህል እስረኞችን የማንጎበኘው ለምንድን ነው? ይህ አግባብ አይደለም መብታችንንም ለመጠየቅ ነገ የታሰሩበት ቦታ ድረስ ሄደን አቤት እንላለን» በማለት ገልፀዋል።

አፍሪካ ኮንፊደንሻል መጽሄት ግንቦት 7 ንቅናቄን አስመልክቶ ባለፈው ሀሙስ ጥያቄ ያቀረበላቸው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ንቅናቄው የራስ ምታት ምንጭ እንጂ ከዛ በላይ ሊሆን እንደማይችል አብራርተዋል። አያይዘውም መንግስት መከላከያን ጨምሮ በሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የማሻሻያ ፕሮግራም እያካሄደ መሆኑን ገልጸው «በአካል ጉዳት፣ በቁርጠኝነት ማነስ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች እኛ ላቀድነው አላማ ብቁ አይደሉም ብለን ያሰብናቸው ሰዎች ሰራዊቱን እንዲለቁ ወይም ማዕረጋቸው ዝቅ ተደርጎ ሰራዊቱ ውስጥ እንዲቆዩ ተጠይቀው ነበር» ካሉ በኋላ «ደስተኛ አለመሆናቸውን የገለጹበት መንገድ፤ በመከላከያ ያሉትንና በሌሎች የመንግስት ሀላፊነቶች ላይ ያሉ ባለስልጣናትን ለመግደል እስከ መሞከር ጥግ መሄዱ ያስገርማል» ብለዋል። ባለፉት ጊዜያት ፣ እንደ አል-ሸበብና አል-ኢትሀድ ያሉትን እውነተኛ ፕሮፌሽናል አሸባሪዎችን መክተናል፣ ያሉት አቶ መለስ «እነ አልሸባብ አደገኞችና ሽብርተኝነትን በተመለከተ አስፈላጊው ስልጠና የቀሰሙ ናቸው። ቡድኑ (ግንቦት 7) እንደነ አል-ሻባብና አል-ኢትሀድ ለእኛ ከባድ ፈተና አይደለም። ጥቃቅን እንቅፋቶችን ይፈጥር እንደሆነ እንጂ በጨዋታው ህግ ላይ ተጽእኖ ያመጣል ብዬ አላስብም፤ ማለታቸው ይታወሳል።